'ክፍል 3፡ የመምህራን ዝግጅትና ምልመላን' እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ። በቅድሚያ የ 'ሮድማፕ አዘጋጆችን አስተያየት ነጥብ በነጥብ (ብሌት ፖይንት) ቀጥሎ የኔን ተጨማሪ አስተያየት በዝርዝር በማከታተል እንድታስተያዩት ይቀል ዘንድ አቅርቤዋለሁ።

**የመምህራንን ዝግጅትና ምልመላ በተመለከተ**

**1 ምልመላ**

- ሁሉ-አቀፍ ማለትም የምልመላ፣ የመረጣ፣ የሥራ ላይ ሥልጠና፣ እውቅና የመስጠት፣ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ፣ የሥልጠና እድል፣ የማልማት፣ የሙያ ፍቃድ፣ ዝውውር፣ አገልግሎትን የማቋረጥ ፣ ወዘተ. ያካተተ መምህራንን የሚያዘጋጅና የሚያለማ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- እጩ መምህራንን 12ኛ ክፍልን የተሻለ የመማር ውጤት ካመጡት ውስጥ መምረጥ፣
- በዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምደባ ወቅት የመምህርነትን ሙያ እንደ አንድ የሥልጠና መስክ ማካተት፣

በመሰረቱ ሁሉ-አቀፍ መምህራን ነክ ጉዳዮችን ያካተተ መምህራንን የሚያዘጋጅና የሚያለማ ፖሊሲ በማዘጋጀቱ በመስማማት የሚከተሉትን አዲስ ሃሳቦች ለማቅረብ እሻለሁ። ማስተማር እንደማንኛውም ሙያ ብቃት ባላቸው ሙያተኞች መሞላት ይገባዋል።

በአለም ዙርያ እንደተለመደው እጩ መምህራንን ከ12ኛ ክፍል መልምሎ አራት አመት በፔዳጎጂካል ሳይንስ ትምህርት አስመርቆ የአንደኛ፤ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ መምህራን እንዲሆኑ ማድረጉ የተሻለ አስተማሪዎች ብሎም የተሻሉ ተማሪዎችን ማፍራት ይቻላል። ከራሴ ልምድ እንዳየሁት፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፔዳጎጂካል ሳይንስ በመመረቁ በእንግሊዝ (ሊድስ ዩኒቨርሲቲ)በጊዜው ከነበሩት 5 ምርጥ ከተሰኙት ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ነበር በኢዱኬሽን:: እንደዚህ ያለ ዩኒቨርሲቲ ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር በወቅቱ ራሴን ሳወዳደር እበልጥ እንጂ አላንስም ነበር። ለምን ብትሉ በኔ ጉብዝና ሳይሆን በወቅቱ የተማርኩት ትምህርት ጥራቱን የጠበቀ ስለነበረ ነው። ይህም የእንግሊዝ አገር ትምህርት ለአዲስ ነገር፣ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ የስራ ባህል ተጋላጭነት ስለሰጠኝ አውስትራሊያ በግሌ እስኮላርሺፕ ማግኘትና በግሩም ውጤት ለመጨረስ አስችሎኛል። ለምን ቢባል በአካዳሚ አፍ ፔዳጎጂ የተማርኩት ትምህርት ጠንካራ መሰረት ስለሰጠኝ መሆኑን አልጠራጠርም። በስራውም አለም (18 አመት አሜሪካ፤

3 አመት አውስትራሊያ አስተምሬአለሁ) ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ከተመረቁ ሰዎች ጋር ያለኝን የስልጠና ልምድ ስንከፋፈል የኔ ይበልጥ እንጂ አያንስም። ለምን ብትሉ ጠንካራ፣ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት፣ ጥሩ ስልጠና የነበራቸው መምህራን እና የኔም ፍላጎት ስለነበረበት ነው።

ስለዚህ የመምህራን ኮሌጆች የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ቅድመ መደበኛ ትምህርት አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ማስተማር አለባቸው። እኔ እራሴ አሁን በትርፍ ጊዜዬ ከሰኞ እስከ አርብ ከፕሪኬ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያሉ ተማሪዎችን በዶክተር ነጋ የትምህርት ማእከል አስተምራለሁ። በቀሪው ጊዜዬ በዋነኝነት በኢንተርኔት (ኦንላይን)የማስተርስና የዶክትሬት ተማሪዎችን አስተምራለሁ። ስለዚህ አሜሪካ ያለውን የትምህርት ስርአት ከላይ እስከ ታች የማውቀው፣ በንድፈ ሃሳብና በንባብ ብቻ በተገነባ እውቀት ሳይሆን እለት በእለት በተግባር በተገኘ ልምድ ላይ የተመሰረተና የተገኘ መሆኑ ይታወቅልኝ።ከዚህ በታች የምሰጠው አስተያየት በተግባር ባለፉት 5 አመታት ካገኘሁት በመነሳት ነው።

በፌደራል የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤ ከናንተ ጋር በከፊል የምስማማበት የሚሆነው " እውቅና የመስጠት፣ የሥልጠና እድል፣ የማልማት፣ የሙያ ፍቃድን ያካተተ መምህራንን የሚያዘጋጅና የሚያለማ ፖሊሲ ማዘጋጀት" በሚለው ነው። የፌደራል የትምህርት ሚኒስቴር እስትራቴጂያዊ ጥቅም ባላቸው ጉዳይ ላይ ዋናው ስራ ማተኮር ይኖርበታል።

በፌደራል ደረጃ እያንዳንዱ ተማሪ በአንድ ማመልከቻ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ማመልከቻው የሚደርሳቸውን አፕ (app) ማሰራትና ለዩኒቨርሲቲዎች እንዲጠቀሙበት አክሰስ መስጠት።

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ፤ የተማሪ ምልመላ፣ አመዳደብ፣ የመምህራን ምልመላ፣ ቅጥርና አገልግሎትን የማቋረጥ ሃላፊነት ለዩኒቨርሲቲዎች መተው የሚገባ ስራ ነው። የምልመላና ምደባ ስራ በዩኒቨርሲቲዎችና በተማሪዎች የሚደረግ ድርድር እንጂ በፌደራል የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የሚደረግ መሆን የለበትም። ካልሆነ ግን ገንዘብና ግንኙነት ያላቸው ተማሪዎች ደህና ቦታ ሲመደቡ፤ የጉቦ ጉልበት ያነሳቸው የማይፈልጉትን ትምህርትና ቦታ ሄደው መማር ግድ ይሆናል። በዘመድና በትውውቅ መስራትም በእጅጉ ይቀንሳል።እንዲህ ከሆነ ዩኒቨርሲቲዎች አቅም የመገንባት ክሎት ይኖራቸዋል።ዩኒቨርሲቲዎች የተሻሉ ተማሪዎችን ለማግኘት፤ እርስ በርስ በመወዳደርና የተሻለ መህስቦች (perks) ለተማሪዎች በመስጠት ወደ እነሱ እንዲመጡ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

በተማሪ ደረጃ፤ እያንዳንዱ ተማሪ በችሎታው የሚፈልገው ትምህርት የመማር፤ የሚፈልገው ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድል እንዲኖራቸው ይገባል። ይህን አይነት በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር ተማሪዎችም በትምህርት ላይ እንዲያተኩሩ

ያደርጋቸዋል። ምልመላንና ምደባን በተመለከተም ፍትህአዊነትና እኩልነትም ይሰርጻል። ያልፈለጉትን ትምህርት አልፈለጉበት ቦታ ሄዶ ተማሩ ማለት ትርፉ ወጪ ነው።

### 3.2 የመምህራን የሥራ ምደባና ዝውውር

- *የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝውውርን በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት እንዲሠራ ማድረግ፣*
- *ብዙሃነትን በሚያጐለብት መልኩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ምደባ ፖሊሲ ማስተዋወቅ፣*

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከስራ ባልደረቦቼ፣ አክብሮት በተሞላው መልኩ፤ ለየት ያለ ሃሳብ ማቅረብ እወዳለሁ። እንደኔ ከሆነ በሰለጠነው አለም እንደሚደረገው የመምህራንን ዝውውር ሆነ ምደባ ለመምህራን የተተወ መሆን አለበት። መምህርነት የውትድርና ስራ ስላልሆነ መምህራኑ የተሻለ እድል የተገኘበት ቦታ የመስራት መብታቸው መጠበቅ አለበት። የስራው ገበያ (labor market) ማስተካከል (regulate) ማድረግ አለበት። የመምህራን ሙያ ሊከበር የሚችለው የመምህራን ልዩ መብቶችና ጥቅማጥቅሞች ሲከበሩ ነው።

በፌደራል የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤ የሁለተኛን ደረጃ መምህራንን ምደባ ፖሊስ ማስተዋወቅ።የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝውውርን በተመለከተ ግን ሚኒስትሩ እጁን ማስገባት የለበትም።

በእስቴት ደረጃ፤ እያንዳንዱ እስቴት ይጠቅመኛል የሚለውን የሰለጠነ መምህር በጥሩ ገንዘብና መሳቢያ የመመልመል ሃላፊነት ይኖርበታል።
በመምህራን ደረጃ፤ ዝውውርንና ምደባን በተመለከተ መምህራን ዋንኛ ባለድርሻ ስለሆኑ በመላው አገራችን በፈለጉበት ቦታ የተሻለ ጥቅማጥቅሞች በሚገኙበት ቦታ ሄደው መስራት መቻል አለባቸው። ካልፈለጉም የመልቀቅ መብታቸው እንደተጠበቀ ይሆናል በስምምነቱ መሰረት።

### 3.3 የመምህራን ሥልጠና ተቋማትና አሠለጣጠን

አገራችን እንደ አገር ልትኖር የምትችለው የተማረና የሰለጠነ  የሰው ሃይል ሲኖራት ነው። በትምህርት ላይ ትኩረት ማድረጉ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው።
በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤ በሃገር ውስጥ ካሉትና በውጭ ከሚኖሩት የፔዳጎጂ ምሩቃን የተዋቀረ ስብስብ ፈጥሮ መልሶ-የማሰልጠን (retraining) ዝግጅት ማዘጋጀት። ይህ በአካል (face to face)፣ በኦንላይንና (online) በቅልቅል (hybrid) መልኩ ሊካሄድ ይችላል።ከተጠናከሩ የትምህርት ዲፓርትመንቶች ባሻገር፤ የፔዳጎጂ

አካዳሚዎች ተመስርተው ከፍተኛ የትምህርት ስልጠና የወሰዱ የትምህርት ባለሙያዎችን ማፍራት ይሆናል።ይህ ኢትዮፕያዊያን ምሁራን ከጠቆሙት 'አንድ አገር አቀፍ የመምህራን የምርምር እና የስትራቴጂ ኢንስቲትዩት መመሥረት' ከሚለው ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል።

በተጨማሪ ደግሞ የግል ዩኒቨርሲቲዎች በአስተማሪ የማሰልጠን ሙያ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ፤ ዩኒቨርሲቲዎች ብቃት የሌላቸውን ተማሪዎች መቀበል የስህተቶች ሁሉ መጀመሪያ ነው። መስፈርቱን የማያሙዋሉ ተማሪዎች ባለ ሁለት አመት የዲፕሎማ ትምህርት ወስደው የተሻለ ውጤትና መስፈርት ካሙዋሉ ወደ ዲግሪ ፕሮግራም እንዲገቡ በሩን ክፍት ማድረግ።

የሁለት አመት ዲግሪ የሚሰጡና የአራት አመት ዲግሪ የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ የሚሰሩበትን መንገድ መፍጠር ለትምህርት ጥራት አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በግል (private universities) ደረጃ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች ይሁን የህዝብ ዩኒቨርሲቲዎች ጠበቅ ያለ መመዘኛ ካላሙዋሉ ፈቃድ አለመስጠትና ከተሰጠም ቀጣይነት ያለው በየአምስት አመት የሚታደስ ፍቃድ እንዲኖራቸው ማድረግ። ፈቃድ ያላቸውና የሌላቸው (not nationally recognized)፣ ሙሉ ፈቃድና (nationally recognized) በጊዜያዊ ፍቃድ (recognized with condition) ያሉ በሚል መለያየትና እውቅና መስጠት ለህዝብም ግልጽ ማድረግ።

### 3.4 አሠልጣኞ መምህራን ምልመላ

- የመምህራን አሠልጣኞችን ለመለየት፣ ለማዘጋጀትና ለማልማት የሚያስችል ማእቀፍ ማዘጋጀት፣

በእስቴት ደረጃ፤ እነዚህ ተጠሪነታቸው ለእስቴት የትምህርት ሚኒስቴር የሆኑት የፔዳጎጂ አካዳሚዎች የአሰልጣኞችን መልሶ ማሰልጠን ስራ የማካሄድ አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ አንዱ ግብአት እንዲያደርጉ ማድረግ ይቻላል።

### 3.5 ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ

- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራምን በትምህርት ቤትም ሆነ በኮሌጆች ተቋማዊ ማድረግ፣
- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም የትምህርት አይነት እውቀትንና የማስተማር ዘዴ ዝግጁነት ክፍተቶችን እንዲመልስ አድርጐ እንደገና ማሻሻል፣
- የክረምት የትምህርት ደረጃ ማሳደግ ሥልጠናን በመተው ለተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ብቻ መጠቀም፣
- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም ከደረጃ እድገት ጋር እና ከሙያ ፍቃድና እድሳት ጋር ማስተሳሰር፣

ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ እጅግ በጣም አስፈላጊና አመቱን ሙሉ ለመምህራንና ለአስተዳዳሪዎች እንዲሁም ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በአካል፣ በኦንላይንና በቅልቅል መልኩ ማቅረብ ይቻላል።

በፌደራል ደረጃ፤ የኮርስ ድግግሞችን ለመቀነስ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ በማእከላዊነት የኦንላይን ኮርሶችን፤ የተልእኮ ኮርሶችን ማዘጋጀት

በእስቴት ደረጃ፤ እነዚህን ኮርሶች ለሚወስዱ መምህራን የእርከንና የደሞዝ ጭማሬዎችን ማዘጋጀት።

በመምህራን ደረጃ፤ እነዚህ ኮርሶች ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞችን በተጨማሪነት ሰለሚያመጡ፤ በቀደምትነት ደግሞ ተጨማሪ ክሎትን ስለሚያዳብሩ ተግቶና ተበረታትቶ የተማሩትን በተግባር ተማሪዎች ላይ ለውጥ እንዲያመጣ መጣር።

**3.6 የመምህራን ሥልጠና ደረጃና ጥቅማጥቅም**

- የመምህራን የሥልጠና ደረጃ በተመለከተ፣
    - ለቅድመ-መደበኛና ለመጀመሪያ ትምህርት በ12+3 ደረጃ የሰለጠኑ፣
    - ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-10)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው፣
    - ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (11-12) ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው፣
- የመምህራንን ጥቅማጥቅሞችንና የማበረታቻ ዘዴዎች ማሻሻል፣ ቢያንስ ቢያንስ የመምህራን ደመወዝ ከሌሎች ሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ/ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ፣ ጥቅማጥቅሞችን ማለትም ቤት፣ ትራንስፖርት፣ ነፃ ሕክምና፣ በጡረታ ወቅት ሙሉ ደመወዝ፣ በዝቅተኛ ወይም ያለ ወለድ የብድር

አገልግሎት፣ ወዘተ. ማቅረብ፤ በአስቸጋሪ ቦታ ለሚሰሩ መምህራን አበላቸውን እንዲሁም ሌሎች ፓኬጆችን ማሻሻል፣

የመምህራንን ስልጠናና ምደባን በተመለከተ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት አሁንም እንደምደግመው ከቅድመ ኪንደርጋርትን ጀምሮ በዲግሪ ማድረጉ መሰረቱ የጠነከረ የትምህርት ስርአት ለመገንባት ጠንካራ መሰረት ይሰጠዋል። ከ 3-5 አመት እድሜ ያሉ ተማሪዎች ላይ ኢንቬስት ማድረግ ረዘምና ደጎም ያለ የመልስ ክፍያ (dividend) ይገኝበታል። ይህ ጥሩ መሰረት ያላቸው ተማሪዎች ለማፍራትና ብሎም ጥራት ያለው አርቆ አሳቢ ትውልድ ለመገንባት ይጠቅመናል።

በእስቴት ደረጃ፤ የሰለጠኑ መምህራንን ለመሳብ ከደሞዝ እድገት በተጨማሪ የቤት መስሪያ ቦታ ወይም ኪራያቸው የቀነሱ ቤቶችን ማዘጋጀት ትልቅ መስህብ ሊሆን ይችላል።

የዛሬ 39 አመት አስመራ ተመድቤ በ381 ብር (ከ 500 ብር ደሞዝ)ቀሪ ገንዘብ ሆቴል እየበላን፣ ሆቴል/ፔንሲዮን እያደርን መኖር ስላቃተን አንድ ሰርቪስ ቤት ለሁለት መኖር ተገደን ነበር፤ ከቤት ማጣት የተነሳ። በወቅቱ የዩኒቨርሲት መምህራን ግን አፓርትመንት ይሰጣቸው ነበር እኔ አስመራ ዩኒቨርሲቲ ሳስተምር (1989 G.C.) ለጥቂት ወራት የዚህ ተጠቃሚ ነበርኩ። ይህ ችግር የነበረና አሁንም ያለሰለሆነ ለመምህራን ባቅማቸው ተመጣጣኝ ቤት የሚያገኙበት መንገድ መፈለጉ ጥሩ መምህራን ሙያውን የሚወዱት መምህራን ስራው ላይ ሊቆዩ ይችላሉ።